ዴሞክራሲያ

ዴሞክራሲያ ቅጽ 38 ቁጥር 1 መስከረም/ጥቅምት 2005 ዓ.ም

## ከወያኔ ዴሞክራሲ ከእባብ ዕንቁላል ርግብ !

መስከረም በጠባ ቁጥር ቸር ወሬ ለተበደለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይደርሰዋል ማለት ባንችልም በዚህኛው መስከረም የዘረኛውና አምባገኑ ወያኔ መሪ ካለንባት ሀገርና ምድር በሞት በመሰናበቱ ሕዝብ እሰየው የሚልበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ያወቀ፣ የመጠቁ መስሏቸው አንዳንድ አድርባዮች አረመኔውን ከሰው ቆጥረው፣ ሰው ሲሞት የደስታ ከበሮ አይመታም ሊሉን ቢቃጡም የሀገርና የሕዝብ ጠላት ሲሞት ጭቁን ሕዝብ ያለቅሳል ብሎ መጠበቅ ግን የለበትም:: ተገደውም ሆነ ተደናብረው እንባ ላፈሰሱ እናዝናለቸዋለን እንጂ ቂም አንይዝባቸውም::

የመለስ ዜናዊ ሞት አብዮታዊ ሁኔታ ፈጥሯል ማለት ባይቻልም መሠረታዊ ለውጥን ለማምጣት የሚረዳ ሁኔታ ሊያመቻች መቻሉ ግን የሚታይ ነው:: ይህ ግን በተፈጠረው ሁኔታ የሕዝብ ኃይሎች ሊሰሩበትና ሊጠቀሙበት ከቻሉ ማለት ነው:: ይህ ግን እውን ሆኗል ብለን ለመናገር ገና አልታደልንም:: ተገዶም ሆነ ወዶ ለኢትዮጵያ አጥፊ ለሆነው ግለሰብ እንባ ያፈሰሰ ዜጋ መኖሩን የታዘብን ሲሆን አሳዛኝና ማፈሪያ የሆነው ደግሞ ተቃዋሚ ነን የሚሉት ክፍሎች ለሀገር ጠላቱ እንባ እናፍስስለት ማለታቸው ብቻ ሳይሆን ለወያኔ አዲስ ተለጣፊ ሹም፣ ጊዜ እንስጠው ፣ ዕርቅና ሰላም ይስፈን ፣ ወያኔ ባለራዕይ መሪዎች አሉትና እንናዳምጣቸው፣ …ወዘተ የሚሉ ቃላትን በማነብነብ ሊጎነበሱ ሲዳዱ ማየታችን ነው:: ወያኔ ግን ወግዱ ብሎ አሳፍሯቸዋል:: እሰየው ያሰኛል:: የተፈጠረውን ሁኔታ ለመሠረታዊ ትግል ለውጥ መጠቀም ሲቻል፣ ገዢው ድርጅት በቀውስ ሲናጥ ይህንን ለሕዝባዊ ትግል ለመጠቀም መነሳት ሲገባ፣ የዚህን ዕድል በአጭር ቀጭተው ለተጨነቀው አገዛዝ መተንፈሻ ጊዜ ሊሰጡ የተነሱት በቀላሉ የማይገመት ስህተት ፈፅመዋል ፣ የሕዝብንም ትግል ጎድተዋል::

መለስ ዜናዊ እንደማንኛውም ጭፍን አምባገነን ሙሉ ሥልጣንን በራሱ እጅ አስገብቶና አፍኖ ይዞ መቆየቱ የወያኔ አገዛዝ፣ አዲስ የፖለቲካ አቅጣጫ ለመቀየስ አቅምም ፍላጎትንም አጥቷል:: ከሁሉም በላይ ግን "ከእባብ ዕንቁላል እርግብ አይፈለፈልም" እንዲሉ ወያኔ ያልተፈጠረበትን ዴሞክራሲ ድንገት መለስ ሲሞት ሊላበስ የሚችል አይደለምና ከወያኔ

አገዛዝ ለውጥን መጠበቅ አይቻልም:: ደዌው የግለሰብ ሳይሆን የሁሉም መሆኑን ከአምባገነኑ ሞት በኋላ ጭፍሮቹ በፀያፍ ቋንቋ ሕዝብን እየሰደቡ የለፈፉት ሁሉ በቂ ምስክር ነው:: ፀረ-ሕዝቡ የወያኔ ስብስብ ይዘቱ አንድ ነው:: ይህንን አሌ ያሉና ከወያኔ መንጋ ሀገር ወዳዶችን ለመልቀም ሲቃጡ የነበሩት ያው ሳይውል ሳያድር ማፈር ተገደዋል:: ይህ እንዳለ ሆኖ በወያኔዎቹ መሀል ደግሞ ሲብሰለሰል የባጀው ቅራኔ ብቅ ማለቱና ዛሬም እየተጋጋመ መሆኑ መታወቅ ያለበት ነው:: መለስ ዜናዊ ሕዝብን ብቻ ሳይሆን ጭፍሮቹንም ከፋፍሎ ነው የሞተው:: ክፍፍሉ በመናሩ አቅም አልባውን ምክትል የይስሙላ ጠቅላይ ሚኒስትር ብለው ቢያስቀጥሉትም ማን ግለሰቡን ይነዳዋል የሚለው ግን ዛሬም ለፉክክር ክፍት ሆኖ ይገኛል:: ቀና የሆነና ሁሉን የሚያስማማ የመለስ ራዕይ የሚባል አለመኖሩም ችግሩን ያባብሰዋል:: ከዘረኝነት ውጪ መለስ ዜናዊ ህልም ሳይሆን ቅዠት ያመሰው ግለሰብ እንደነበር የሚክዱት ሎሌዎቹና ባዕዳን ጌቶቹ ብቻ ናቸው:: ሳለው ቅንጭብ ያረግዳል ሆነና ጥራዝ ነጠቁን ዘረኛ አዋቂና ብልህ ብለው በማሞገስ አድርባዮች ቢጮሁም ሕዝብ የሚያውቀው ሐቅ ግን አምባገነኑ በዴሞክራሲና በአንድነት ሕዝብን ለማስተዳደር ያልቻለና ያልፈለገተራ ጎጠኛና ጨፍጫፊ ነው የሚለውን ነው::

አምባገነኖች ደግሞ የሀገራችን አሰቃቂ ዕጣ ሆነው ሲያደሙን ከርመውብናል:: ከነሱም ጋር ባዕዳን እየተፈራረቁ በመሰለፍ ኢትዮጵያን ጎድተዋል:: ሁሉም አምባገነኖች ደግሞ በሥራቸው ቅጥረኛና ባንዳን ለማሰለፍ የቻሉ መሆናቸውም የሚታይ ነው:: በሂደትም የሀገሪቷ ምሁሮች ሚናበሚያሳስብ ደረጃ መለዋወጡንም ሁኔታው እመኑ እያለን ነው:: ከአንጉል ተስፋና ባዶ ምኞት ባሻገር አፍጦ አለሁ የሚለንን ሐቅ በጥሞና ስንመለከተው ዛሬም ቢሆን ከቶም የማይታረቀው ቅራኔ የወያኔን አገዛዝ ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለያይቶ ያለው ነው:: ይህ መሰረታዊና አቢይ ቅራኔ ደግሞ በድርድር ወይም አንዳንዶች ጭንቅ ሲመጣባቸው ሊመክሩእንደቃጡት በውይይትና  በመቻቻል ከቶም ሆነ መቼም የሚረግብ ወይም መፍትሔ የሚያገኝ አይደለም:: ሕዝብ ጨቋኙን እንዲችል መምከር ወንጀል ነው:: በወያኔ አገዛዝና በሕዝብ መሀል ያለው አቢይ ቅራኔ በተሸናፊና አሸናፊ ደረጃ የሚፈታ መሆኑን ማወቅ ተገቢ ነውና:: ይህ የጥላቻ ወይም የአክራሪነት አቅዋም ሳይሆን እንደሬት ቢመርም መጨለጥ ያለበት የሐቅ ፅዋ መሆኑን እወቁ የሚለንም ራሱ ወያኔ ነው:: ዕርቅ ሲሉት የምን ዕርቅ፤ ለወጥ ሲሉት ምን ጎድሎ፤ ድርድር ሲሉት ለአቋራጭ ሥልጣን አትቋምጡ፤ የአማራና የክርስቲያን ጊዜ አከተመ፤ በጀመርነው እንገፋለን፤ የምንለቀው የፖለቲካ እስረኛ የለም፤ …ወዘተ እያለ ካልጣላችሁኝ ካላስወገዳችሁኝ መፍትሔ የለም፤ አይኖርም እያለን ያለው ወያኔ ራሱ ነው:: ለአንበሳ አይመትሩም፤ ለብልህ አይነግሩም ነውና ዓይኑን የከፈተ የማየት፤ ጆሮውን የከፈተ የመስማት ግዴታ አለበት:: ዜጋ ከተደናገረ ሀገሩን ይቀማልና ጠላትን ጠንቅቆ አውቆ ለማሸነፍ አምርሮ መታገል ዛሬም የመጀመሪያ ሀገር አድን ግዴታ መሆኑ መዘንጋት የለበትም::

ባዕዳን ሚቹ ፀረ-ሕዝብ ቡችላቸውና ሎሌያቸው ነበርና ታላቅ ሰው ሞተ ብለው ሊያላዝኑና በቁስላችን ላይ ጨው ሊነሰንሱ ሲሯሯጡም ታዝበናል፡፡ ለሕዝብ ሬት ሬት ያለውን አስከፊ አገዛዝም ሲያደንቁ ተሰምተዋል፡፡ ሚሊዮኖች ለረሀብና አስከፊ ድህነት ተጋልጠው ባለበት የሀገሪቷ ኤኮኖሚ ጋለበ፤ አደገ ተመነደገ ብለው ሲዋሹም አድምጠናል፡፡ ክስተቱ ተመክሮ አዘል ነው፡፡ አንዳንዶች ስርየት ያመጡልናል ብለው የሚለምኗቸው ባዕዳን ምንኛ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ደንታ እንደሌላቸውና በደሉ እንደሚያስደስታቸው አረጋግጠዋል፡፡ ስለዚህም ነጋ ጠባ አሜሪካ አባታችን ሆይ ብለው ፀላዮች ከሰይጣን ፅድቅ አትለምኑ ሊባሉ ይገባቸዋልማለት ነው፡፡ ኢትዮጵያን ማዳን የሚችልና የሚገባው ፤ ግዴታውም ሆኖ የሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው - ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም ተብሎ የለ! የዘረኛው ሞትና የባዕዳን ባለጌ ጫጫታ ሌላ ያጋለጠው ጉዳይ ካለ ማነው ሀቀኛ ሀገር ወዳድ ማነው አስመሳዩ የሚለውን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለሕዝብ ትግል ጠቃሚ ነው ጎራውን ያፀዳልና፤ ለመጠናከር ይችላልና፡፡ ሕዝብ ከጅብ ጎሬ ሸሽቶ ከጅብ ዋሻ እንዳይገባ ከፈለገ በመሀሉ ወይም በጎራው ያሉትን አስመሳዮችና አድርባዮች ማራቅ አለበት፡፡ ፀረ ሕዝቡ መለስ ሞተብን ብለው ሀቀኛ ገፅታቸውን አጋልጠዋል፡፡ ሳይገደዱ ወይኔ ብለው ሲያለቅሱ፤ ለሚቹ ሙሾ ሲደረድሩ፤ ግለሰቡ ስለሞተ ሥርዓቱ ያለቀለት አስመስለው በማቅረብ ሕዝብን ሊያደናግሩ ሲጥሩ፤ ለምን በአምባገነኑ ሞት ተደሰታችሁ ብለው ሊወቅሱ ሊሳደቡም ሲነሱ ፤ የቀድሞ ወያኔዎች ነን ባዮች፣ ምሁሮች፣ ተቃዋሚ በሉን ባዮች፣ ፖጮችና ዘፋኞች፣ ከጀኔቫ እስከ ዋሺንግተን ፤ ከካርቱም--ናይሮቢ እስከ ፈረንሳይና ስዊድን አወስትራሊያ፣ ...ወዘተ ያሉ አንዳንድ ዜጎች ሀገራችንን ላዋረደና ወገኖቻችንን ለጨረሰ አረመኔ ሲያለቅሱና ዋይ ዋይ ሲሉ መሰማቱ፣ መታየቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከታዘብናቸው አሰቃቂ ክስተቶችና ምፀቶች አንዱ ነው፡፡ ታሪክ ይህን በሚገባ መዝግቦ ሕዝብ ነገ ተነገ ወዲያ ጠያቂ በሚሆንበት ጊዜ የሚወራረድ ሒሳብ መኖሩንም ይጠቁመናል፡፡ ጠላትን ማወቅ፤ አስመሳይ ወዳጅንም ማራቅ ተብሏል !

አገዛዞች/ሥርዓቶች ወደ ቀውስ ሲያመሩ ሁኔታው ሁሌም አማራጮችን የሚያቀርብ ይሆናል፡፡ የሕዝብ ጎራ በቅራኔው ተጠቅሞ ጠላቱን ማሸነፍ ከቻለ ለውጥ ይመጣል፡፡ ካልቻለ ደግሞ ወይ የነበረው እንዳለ ወይም በአዲስ ጭምብል ይቀጥላል ወይም ብጥብጥ ይሰፍናል፡፡ በየካቲት 66 የኢትዮጵያ ሁኔታ ነበር በ1983 ደግሞ የሶማሊያ ሁኔታ ነበር፡፡ ሌላም ሌላም፡፡ በቅርቡም ለውጥ ያመጡ ወይም የባሰውን የተኩ ተመክሮዎችን አይተናል፡፡ የመለስ ዜናዊ ሞት ለውጥን ያረገዘ ነው፡፡ ብሩህ ቀን እንዳይወለድ ለማጨናገፍም የታጠቀ ነው፡፡ ነገ ምን ይመጣል ለሚለው መልስ ለመመለስ በአንድ በኩል ሕዝብ በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔና ጭፍሮቹ ግብግብ ዛሬ ገጥመዋል፡፡ በዚህ መሀል ገብተው ሕዝባዊ መስለው ግና የወያኔን አገዛዝ ዕድሜ ሊቀጥሉ የተነሱትን መቃወምና ማስወገድ ወሳኝ ነው፡፡ ውዥንብር ፈጣሪ

ናቸውና፤ የወያኔን አገዛዝ መለስ አልባ ቀጣይ ናቸውና። በተፈጠረው ሁኔታ ሕዝብ በሚገባ ተጠቅሞ ወደ ድልና መሰረታዊ ለውጥ ሊያመራ እንዴት ይችላል የሚለው ጥያቄ ቀዳሚና ወቅታዊም ነው። ፀረ ወያኔ ሳይሆኑ ከወያኔ ጋር ሊቋሸሹ ፍላጎት ያላቸው ሁሉ ዛሬተጋልጠዋል፤ አውቀናቸዋል። በቀውጢው ቀን የመለስና የወያኔ ጠበቆች ሆነው እያለቀሱ ብቅ ብለዋል። እነዚህን ሁሉ ከሕዝብ ጎራ መመንጠር ወሳኝ ነው። እያንዳንዱ ተቃዋሚ ድርጅትም ወያኔን በሚመለከት የሚልፈሰፈሰውንና ክህደት የሚያቀነቅነውን ሁሉ መንጥሮ ማስወጣት አለበት። ግም ለግም አብሮ ያዝግም እንጂ ከሕዝብ ጎራ ማቀፉ ምን ይባላል? የዛሬ ወሳኝ ወቅት በዚህ በዚያ መንገድ በየትኛው ጉዞ ባይ ነውና ምን ማድረግ ይገባል--አለብን የሚለው ታሪካዊ ጥያቄ መቅረብ አለበት። ዛሬ በዚህም በዚያም ወቅታዊውን ሁኔታ ስንመረምረውና ስናጤነው መላው ሕዝብ ከወያኔ ሥርዓትና አገዛዝ ጋር ያለው የማይታረቅ ቅራኔ ዋና ነኝ ይለናል። ማለትም የወያኔን አገዛዝ በታቸለውና በሆነው መንገድ ማቸነፍ ፤ ማውረድና ወደ እንጦርጦስ መስደድ ተልዕኳችን ሆኖ ይገኛል። ይህን ተግባር የሚያወግዙ ወይም ከወያኔ ጋር መተቃቀፍን የሚሰበኩ ሁሉ የሕዝብን ትግል ቅኝት ሊያበላሹና ሊያኮላሹ የተነሱ ናቸው። በአሁኑ ወቀት በኢትዮጵያ ዜጎች ለመሰረታዊ መብታቸው ሰልፍ አያደረጉ ናቸው። ማነው እነኚህን ዜጎች በተጨባጭ የደገፈው? ማነው በየአርቡ ከሙስሊም ኢትዮጵያውያን ጋር በመሰለፍ ተቃውሞ ያሰማው ? አስተማሪው የደሞዝ ጭማሪ ጥያቄ የለውም ? ብዙሃኑ የኑሮ ወድነት ተቃውሞ የለውም ? ዜጎች ሀገራችን ለባዕዳን ተሸጠች ብቻ ሳይሆን ተሰጠች፤ ቋራ ለሱዳን ተሰጠ፤ ዋልድባ ተደፈረ፤ ጋምቤላ ተሸጠ፤ ... ወዘተ በሚል ምሬት የላቸውም? ታዲያ ለምን አይሰለፉም ? ለምንስ ሙስሊም ዜጎቻችንን አጅበው ተቃውሞ አያሰሙም? ለምን? መጠየቅ ያለበት ነው። ለለውጥ አመቺ ሁኔታ ሲከሰት ሕዝብም ይህን ሊጠቅምበት ካልተረባረበ ሁኔታው ይተናል። ካለፈም መቆጨቱ ፍሬ አይኖረውም። በጠገበኩ እኮ ጠብ የለም። የተበደለ፣ የተራበ፣ የተጨቆነና መብቱን የተነጠቀ ሕዝባችን እምቢኝ፣ በቃኝ ብሎ ማመፅና ወያኔን ማሸበር አለበት። ከዚህ በላይ ምን በደል፣ ምን ውርደት፣ ምን መከራ ሊመጣ?

በወያኔ/ኢሕአዴግ ሰፈር ያለውን ሁናቴ በጥሞናና በትኩረት ለሚመለከት በውስጡ እየተባባሰ ያለው ቀውስና በዚህም ሳቢያ በአባላቱ በተለይም መካከለኛና ከፍተኛ ሥልጣን በያዙት መካከል ያለውን ንትርክ ከምንጊዜውም በላይ እየደከመ መሄዱን የሚያመላክት ነው። ይህ ሁናቴ ከመለስ ሞት በፊትም የታየ ቢሆንም ከሕልፈቱ በኋላ ግን እየተባባሰ መሄዱ በግልሥ የሚታይ ነው። በድንገተኛ የጄኔራሎች ሹመት የስብሀት ነጋ ቡድን የበላይነት ሲይዝ በነበረከት ሠፈር ጥቃት መድረሱ የዚሁ የቀውሱ ውጤት መሆኑን የሚያመላክት ነው። ወያኔ የአፈና መዋቅሮቹን በጁ ቢሆኑምና የሮንዳንድ ኃያል አገሮችን ድጋፍ ቢያገኝም የሕዝብ ድጋፍ ግን ጨርሶ የለውም። በመሆኑም መፍትሄ ሊገኝለት በማይችለው ቀውስ ውስጥ ተዘፍቋል። ብዙሃኑ ሕዝብም ጠልጦት ለውድቀቱ የበኩሉን

ጥረት እያበረከተ ይገኛል:: በሃይማኖት፣ በብሔረሰብ፣ በአካባቢ፣ ...ወዘተ ወያኔ ሕዝብን እርስ በርሱ ለማናከስና ለማጋጨት ጥረት እድርጎ ባንዳንዱ ላይ ጉዳትን ቢያደርስም እቅዱ አልተሳካለትም:: የሙስሊሙ ኢትዮጵያውያንን ፍትኃዊ ተቃውሞ አጣሞ ሊያቀርብና ክርስቲያኑን ሊያስፈራራ ሊያስጨንቅ የሞከረውም ፍሬ አልባ ሁኗል:: ዘረኛው አገዛዝ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ በሕዝብ ተጠልቷል:: የሕዝብ ተቃውሞም እየጎለበተ ነው:: ኃይለማርያም ደሳለኝ በመለስ እግር ከተተካ በኋላም እየወሰዳቸው ያሉት ተግባራትና በተለይም በቅርቡ በምክር ቤት ተብየ ስብስብ ውስጥ የተናገራቸውና የሱ አገዛዝ ወደፊት ለመተግበር የወጠናቸውን ላየ፤ የተከሰተው ቀውስ ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚችል ይገነዘባል:: ለውጥ ሮዘል ቀውስ ዳምኖ ባለበት በአሁኑ ጊዜ ገዥቀ ክፍል ባለፈው መንገድ ሊገዛ ወይንም ሊቀጥል እያቃተው መምጣቱም የሚታይ ነው:: ስለሆነም ምን ማድረግ አለብን ስንል፣ ታሪካችንን የምንዳስስበት ወቅት ላይ መድረሳችንን ተገንዝበን ለወቅቱ የሚመጥን የትግል እስትራተጂ ነድፈን የወያኔሂ አምባገነን አገዛዝን ታግሎ ከማቸነፍ ውጭ ሌላ አማራጭ የለም:: በመሆኑም ለኃ/ማርያም ጊዜ እንስጠው፤ ዕርቅ እንሻ፤ መሠረታዊ ለውጥ ብለን አናከር ባዮች የሕዝብን ሳይሆን የግላቸውን ጥቅም በሱም ሳቢያ የባዕዳን ደጋፊዎቻቸውን ጥቅም በሀገራችን ለማስከበር የሚንቀሳቀሱ ናቸውና ሰሚ ጆሮ ሊሰጣቸው ጨርሶ አይገባም እንላለን::

ስላለው ጭንቅና መከራ ማውሳቱ ተደጋጋሚ ስለሚሆን ዋናው ትኩረታችን ምን መደረግ ይገባዋል በሚለው ላይ መሆኑ የተሻለ ይሆናል:: ወደፊት ለመጓዝና የትግል ጉዞን አቅጣጫ ለመቀየስ ይረዳልና:: ወያኔዎች እርስ በርስ ቢተራመሱም ለሌሎች ቀዳዳ ላለመክፈትና ለአደጋ ላለመጋለጥ በሚል ጊዜያዊ ቢሆንም ስምምነት እያደረጉ ናቸው:: ባይሆንማ ኖሮ የለየላቸው የወያኔ የርስ በርስ ህብረት ጠላቶች (ስብሀት ነጋ፣ ስዩም መስፍን፣ በረከት፣ አዲሱ ለገሰ፣ ...ወዘተ) ሰምረውና የጋራ ጠላቶች መጡብን በሚል አንድ አቋም በያዙ ነበር:: ሥልጣን ጤነኛውንም ሆነ የለቀቀውን ለዕብደት ጋባዥ ናትና ማንኛውንም ማስተናገድ ደግሞ ሥራዋ ነው:: በወያኔ ውስጥ የተከሰተው ትርምስ በራሱ ጎዳና የሚጓዝና ምናልባትም ለወያኔ አገዛዝ ውድመት በቀላሉ የማይገመት አስተዋፅዖ የሚያደርግ ይሆናል:: አዝማሚያው ይታያል ግና ጉዳቱ እውን ይሆን ዘንድ ደግሞ ከሕዝብ ጎራ ግፊትና በል በለው፤ ተባባል ማለቱ አስፈላጊ ይሆናል:: የወያኔ አገዛዝ ጠላት ነው ብሎ በተቻለ ህብረት ማጥቃት ሲገባ የለም አሁንም ቢሆን ብልህና ባለ ራዕይ ሰዎች በውስጣቸው አሉና ድርድርን እንሻ ብሎ አጉል አቅዋምን መያዙ የሕዝባችንን ትግል በጣም ጎጂ ነው:: በመጀመሪያ ወያኔዎች የነጮች ሀገር አጥፊ ቅዠት እንጂ ሀገርን ጠቃሚ ራዕይ የላቸውም:: ወያኔዎች ዘረኛ ናቸው::

ያለውንና የሆነውን በሚገባ መመርመር ጠቃሚና አስፈላጊ ቢሆንም ዋናው ቁም ነገር ግን

ምን ማድረግ አለብን ፤ ምን መደረግ አለበት ፤ ድል አብሳሪው ትግል እንዴትስ ይካሄዳል የሚለው ነው። ገዢው ቡድን አንዳለፈውና አንደቀየበት ሊገዛ ሊጨቁን ይፈልጋል። ነገሮች መለዋወጣቸውን ቢረዳም ያደቆነው ሰይጣን አለቀው ብሎታል በሕዝብ ላይ ንቀቱን እያጠናከረ ለዘመናት በሀገርና በሕዝብ ላይ መጨፈር ይመኛል። ይህ ደግሞ ከሕዝብ ፍላጎት ጋር ከቶም የሚገጥም አይደለምና ያው የአገዛዙ መስመርና ፖለቲካ በአፈናና በግድያ የሚታጀብ መሆኑ አያጠራጥርም። ሕዝብን ለማባበልና ለማንቆሻበል ወያኔ ትዕግሥቱም ፍላጎቱም የለውም። ማሞኘትና መደለል አሊያም ከፋፍሎና ረግጦ መግዛት የሚለው ነው በተሻለ የወያኔን ማንነት ገላጭ። ወያኔ ወደደም ጠላም በወያኔነት ዛር ተይዞ ተፈራጋጭ ነውና የተቀየረና ሊያሻሽል የሚጥር አስመስለው ሊያቀርቡት የሚጥሩት አንድም ተሳስተዋል አሊያም በጥቅም ተገዝተዋል። የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች የሚባሉት--የቀድሞ ወያኔዎች የሚባሉትንም ጨምሮ -- ከአገዛዙ ጋር በጥቅም መያያዛቸው ምስጢር አይደለም። ይህ ደግሞ የቆሰለ ውሻ አምርሮና አጥብቆ አይጮህምን ያነሳል። ይህ ደግሞ በቀድሞና በዛሬ የተቃዋሚ መሪዎች መሀል ያለውን ባለሚዛን ልዩነትንም ይጠቁመናል።

ዛሬም ዕርቅና ስምምነት የሚሉ አልታጡምና ይህ መንገድ ከቶም የማይሰራና ተቀባይነትንም የማያገኝ መሆኑን ወያኔ ራሱ ዳግም ጫና ሰጥቶ ገልጦታል። እንኳን ከሌላው ተቃዋሚ ከራሳችንም ከወጡት የቀድሞ ጓደኞቻችን ጋር ዕርቅ ዘበት ነው ብለው በተለይ አሜሪካ አውጠንጥኖት የነበረውን አስመሳይ የለውጥ ሂደት ወያኔዎቸ በእምቢታ በአፍጢሙ ደፍተውታል። የመለስ ዜናዊ ቅርስ ጭፍን ወያኔነት ነውና ቅርሱን እናከብራለን ባዮቹ በድንገት የዴሞክራሲያዊነት ህልም ሊወዘውዛቸው ከቶም አይችልም። የዘሬን ብተው ይዘርዝረኝ ነው ሐቁ--የጅምላ ግምትን ማስተናገድ ባንወድም። በመሆኑም ሀገር ወዳዱ ኃይልና ሕዝብ ይህን ሥርዓትና አገዛዝ ለማስወገድ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ለመታገል መነሳት አለበት። ሌላ አማራጭ የለም--ቢኖርማ ደስ ባለን ሁላችን። ከወያኔ ሌላ ሰላምን የሚጠላ ኃይል የለም። ያለውን አገዛዝ--ያ ይህ ወያኔ የበላይነትን ያዘ አልያዘ--በትግል ማስወገድ አማራጨ አልባ ነው። እነ ጊዜ እንስጥ መብትንም ሀገርንም አሳልፎ ከመስጠት ሌላ ምንም ውጤት መቸም አላስገኙም። ለእንዳልካቸው ጊዜ እንስጠው ፤ ለደርግ ጊዜ እንስጠው ፤ እነ መለስ ልጆቻችን ናቸውና ጊዜ እንስጣቸው ፤ ለአዲሱ የወያኔ ቡችላም ጊዜ አንስጠው--ይህ ሁሉ መልዕክቱ መብታችንን እንስጣቸው ፤ሀገራችን ኢትዮጵያን አሳልፈን እንስጣቸው ነው። ሽንፈት፤ አድርባይነት፤ ባንዳነትና ሀገር ጎጂነት!

ይህን ሁሉ ተረድተን በሀገር ማዳኑ ግዳጅ ለመሰለፍ መቁረጥና ማድረግ ያለብንን ለማድረግ መነሳቱ የግድ ይሆናል። ስለ ትግል ብዙ ተሰልቋል--ተጨባጭና ተግባራዊ ትግል ላይ ግን የነበረንን ድክመት መካድ አይቻልም። ለዚህም ነው ከትግል ወሬ ቀነስ አድርጎ ተግባራዊ

ስምሪትን ጠንከር ማድረግ የሚገባው:: ይህን በተመለከተ ትግሉ በተባበረ መንገድ ቢካሄድ ይበልጥ ውጤታማ መሆኑን ማንም ሊክድ አይችልም:: ግን የህብረት ጉዳይ ዛሬም ውስብስብ እንደሆነ ማመን ደግሞ የግድ ነው:: ህብረት ብለው ሲነሱ ግባቸው ላይ ስምምነትና አንድ ወጥ አቅዋም ባለመኖሩ ተባበርን ባሉ ማግስት ፍርሻ የተለመደ ሆኖ ቆይቷል:: አሊያም ቢወቅጡት እምቦጮችና ሚዛን አልባዎች አበርን ይሉና ሚዛናቸው ገለባ ሆኖ ይቀራል:: ሌሎች ደግሞ የሚያብሩት ራሳቸውን ለወያኔ አስማምረው ለማቅረብ ይሆንና አመርቂ ውጤት አይኖራቸውም:: ህብረቱ በተጨባጭ ትግል ስምሪት በሀገር ቤት መሆን አልቻለም እስካሁን:: የተቻለ ቀን ግን የወያኔ አገዛዝ ይናጣል፤ ይሸበራል፤ ይነቀነቃልናምወደ ውድቀቱ ያመራል:: ይህ ከድርጅቶች ሲጠየቅ ከሕዝብ ደግሞ ቆርጦ መነሳትን መጠየቅ ተገቢ ነው:: የሕብረተሰቡ የተወሰነ ክፍል ወያኔን ሲቃወምና ሲፋለም በዝምታ ማየት ሳይሆን ትግሉን መደገፍና በትግሉ መሳተፍም ከሕዝብ ይጠበቃል:: ሀገሩን የሚያድን ሕዝብ ነው:: ኢትዮጵያ ከወያኔያዊ ጥፋት የምትድነውና ከነዚህ አረመኔዎች የምትላቀቀው ሕዝቧ ከታገለላትና ከተሰዋላት ብቻ ነው::

በአንድ ሀገር ውስጥ ለሰላም መገኘትም ሆነ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማስፈን በተለይ የሕብረተሰቡ ግማጽ አካል በሆኑት በሴቶች ካልተደገፈ የሚገኘው ውጠት መሠረቱ የተበሳሳና ዘላቂነትም እይኖረውም:: “የሴቶች መብት ይከበር! የሴቶች እኩልነት በተገባር ይረጋገጥ! በተለያዩ ማኅበራዊና ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ መድረኮችና ተቋሞች ውስጥ መብታቸው ይጠበቅ! ...” የተሰኙት መፈክሮች ለይስሙላና ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሲባል እንደወያኔ በአፉ ብቻ የሚነገሩ ሳይሆኑ ለኢሕአፓ ወሳኝ መልዕክት ያላቸው ናቸው:: የሴቶች መብትና ጥቅም ሳይከበርና በተግባርም ሳይረጋገጥ የሕዝባችን ብሔራዊ ደህንነትና እድገት ይገኛል ማለት ዘበት ነው:: የዴሞክራሲና የነፃነት መብቶች ባልተከበሩበት ህብረተሰብ ውስጥ ደግሞ ለነዚህ መሟላት የሚደረጉ ትግሎች ከግብ አይደርሱም:: ስለሆነም ደጋግመን እንደገለጽነው፣ የሕብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን የእናት፣ የእህቶቻችንን ልብ፣ ስሜትና እምነት በሚገባ ያላገኘና የነሱንም የትግል ተሳትፎ በተግባር ለማረጋገጥ ካልተቻለ በትግሉ የተጠበቀውን እድገት ለማግኘት እስቸጋሪ ነው:: ስለሆነም ሴቶችን በፆታዊ ጥቅማቸው (መብታቸው) ላይ በመመስረት ማደራጀት፤ እያደራጁም ማታገል፤ እያታገሉም ከግብ ለመድረስ ወሳኝ ነውና በዚህ እንቀጥልበታለን::

ከወያኔ ጥፋትና ዕልቂት እንጂ ደግ አይጠበቅም!
የወያኔን አገዛዝ ለማውደም በጋራ እንነሳ፤ እንታገል!
እናቸንፋለን !!